# የግንቦቱን ወጥመድ፣ ትውልድ ሲፋረድ

(ከነቅዓ ጥበብ)

ያን ጊዜ በግንቦት፣ በዘጠና ሰባት፣
ትንሽ በር ተከፍቶ፣ እንደ ልብ ለማውራት፣
ሁሉም ተነፈሰ፣ ብሶቱን ለማውራት፣
ወያኔም ወዳጁን፣ ጠላቱን ለየበት።

ግፍ ያንገፈገፈው፣ ሁሉም አመረረ፣
መፍራት መሸማቀቅ፣ በዋለበት ቀረ፣
ቀስቃሽ ቀሰቀሰ፣ ምሁር አስተማረ፣
ጋዜጠኛ ተቸ፣ ሀቁን አበጠረ፣
ተቃዋሚው ሁሉ፣ በጋራ ዘመረ፣
ወጣት አዛውንቱ፣ ባንድ ልብ መከረ፣
ገጠር ተከተማ፣ ሕዝብ ተባበረ።

ሆኖም ግን ኢሀአዴግ፣ ውስጡን እያሴረ፣
ዓለምን በሙሉ፣ ሊሸውድ ሞከረ፣
ታዛቢን ጋበዘ፣ ቃሉን አሳመረ፣
“ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ”ን እያመሳጠረ፣
እንከን እንደማይኖር፣ ደጋግሞ ፎከረ፣
ሕዝቡን ግን ቀደመው፣
ወያኔ ተዳከሞ፣ ወደሁዋላ ቀረ።
በመሬት አንቀጥቀጥ፣ የሰልፍ ማዕበል፣
ኢሀአዴግ ሰጠመ፣ ሜዳው ሆነ ገደል፣
እንደ ገሞራ እሳት፣ ሕዝቡ ሲገነፍል፣
የወያኔ ካድሬ፣ ባንዳው የኮር አባል፣
አውደልዳዩ ሁሉ፣ በያለበት ቀጥኗል።

ሰላማዊ ዜጋ፣ በሰላማዊ ሃይል፣
ማንነቱን ገልጧል፣ ያለማወላወል።
ያ ሰላማዊ ሕዝብ፣ መቼ በሰልፍ ብቻ፣
በድምጽ ሲያጠቃም፣ ምንም የለው አቻ!
ቀንበሩን ለማውለቅ፣ ያለቅጥ ጎምጅቶ፣
ቁርስና ምሳውን፣ እራቱን እረስቶ፣
ተራውን ጠብቆ፣ እንቅልፉን ሰውቶ፣
ትንፋሹን ዋጥ አርጎ፣ በካርዱ አነጣጥሮ፣
በየመሸገበት፣ ወያኔን ሰባብሮ፣
ባለመሳሪያውን፣ በድምጽ ብቻ ጥሏል፣
ግዳዩን በቀመር፣ ከምሮ አስመዝግቧል፣
ሀቅ አንድ ብቻ ናት፣ ማን ያስተባብላል?!?!
ታዛቢ ባለበት፣ የጦር ግንባር ሁሉ፣
ሕዝቡ አቸንፎ፣ ተደምድሟል ድሉ!

በዴሞክራሲ ስም፣ መሸንገል ሲፈልግ፣
ወያኔ ተረትቷል፣ እርሱ ባወጣው ህግ፣

የሚሳነው የለም፣ ሰፊው ሕዝብ ሲታደግ።
በአዲስ አበባ፣ በዋናው ከተማ፣
ለወያኔ ሞረሽ፣ ድምጽም አልተሰማም!
ታዛቢ ባለበት፣ የድምጽ ጣቢያ ሁሉ፣
ወያኔን ተፍቶታል፣ መራጩ በሙሉ፣
ታሪኩ ይኼ ነው፣ ቢወዱም ቢጠሉ፣
ሕዝብ የጠላቸው፣ እንዴት ያስጠላሉ!?

መለስም ሲናገር፣ ነገሩ ተሰምቶት፣
"ለምን ድምጻችሁን፣ ለእኛ ላለመስጠት፣
እንደወሰናችሁ፣ ገብቶናል በቅጽበት፣"
በማለት መስክሯል፣ ሲናገር በምጸት።

ወዲያውም ቁርጡን ሲያቅ፣ ሂሳቡን ቀምሮ፣
ገና የምርጫው ካርድ፣ ሳያልቅ ተቆጥሮ፣
በሶስት መቶ ሃያ፣ ስድስትን ጨምሮ፣
"እና አሸንፈናል፣ ምርጫውን ዘንድሮ፣
ሰልፍ የሚባል የለም! ከዛሬ ጀምሮ!
ጦሩም በእኔ ስር ነው፣ ሁሉም ተደምሮ፣
አንድ ሰው እንዳላይ፣ እጣቱን ቀስሮ፣
የሰዓት እላፊም፣ አዋጅ አውጥተናል፣
ወይ ትንፍስ! ወይ ንቅንቅ! ይኸው ተናግረናል።"
አለና ደስኩሮ፣ መለስ "ዴሞክራቱ!"
ዴሞክራሲን አንቆ፣ በሕፃንነቱ፣
ትንፋሹን አጠፋው፣ ተለየ ሕይወቱ።

አንዱ ሰው ፓርላማ፣ ብሔራዊ ሸንጎ፣
ሆኖ በመወሰን፣ ብቻውን ደንግጎ፣
ፍለጠው! ቁረጠው! የሚልበት አገር፣
በየት ይገኝ ይሆን?! ከኢትዮጵያ በቀር?!
ሕዝቡን በጣም ንቆት፣ ባበጠው ትዕቢቱ፣
አፍህን ያዝ አለው፣ እንደ ልጅነቱ!
የእንከን የለሽ ምርጫ፣ ይህ ነው ምልክቱ?!

ግን የሕዝብ ቁጣ፣ ብሶት ሲፈነዳ፣
በምን ይመረጋል?! መች ያጣል ቀዳዳ!
የኮረጆ ሌቦች፣ ድምጹን ሲሰርቁበት፣
እንደምን ይነሰው፣ ሌባ! ሌባ! ማለት?!

ያን የሕዝብ ቁጣ፣ የነፃነት ብሶት፣
ተቃዋሚ ቢጥርም፣ በሰላም ለመፍታት፣
አሻፈረኝ ብሏል፣ ወያኔ በዕብሪት፣
"ከሌባ ጋር ጠበል፣ አትጠጡ" ቢሉ፣
ዘርን የሚያጠፋ፣ የቱ ነው ወንጀሉ?!

የወያኔ ትዕቢት፣ አልበርድ ስላለ፣
ከተማው በሙሉ፣ ባንድ ቀን ጸጥ አለ።
በወያኔ ስብከት፣ እንዳይዘናጉ፣

የታከክሲ ሾፌሮች፣ በራቸውን ዘጉ፣
ሌሊቱም ተባብረው፣ ባሉበት መሸጉ።
ያለው ከሌለው ጋር፣ እየተካፈለ፣
ወቅቱን ለማሳለፍ፣ ድርሻውን ከፈለ፣
ክፉን ቀን ለማውጣት፣ ምን አማራጭ አለ?!

የወላጆቹን ድምጽ፣ ሌቦች ስለቀሙ፣
ተማሪ ተነሳ፣ ሊታደግ በደሙ፣
ዕጣ ፈንታው ሆኖ፣ ገና ከቅድሙ፣
ተማሪ ሲታፈን፣ ወላጅም ቢወጣ፣
አግአዚ የሚባል፣ ከጫካ የመጣ፣
ካውሬ የማይለይ፣ አረመኔ ዓይን አውጣ፣
በማንም ዜጋ ላይ፣ ደርሶ በማጉረጥረጥ፣
ባልቴት ሽማግሌ፣ ሕፃናትን ሳይመርጥ፣
በጥይት፣ በሰደፍ፣ በሳንጃ፣ በቆመጥ፣
ሁሉንም አሰጣው፣ እንደ እንጨት በመፍለጥ፣
ያስር ዓመት ጮርቃ፣ እንቡጦች በመቁረጥ፣
እንደ ፋሽሽት ዘመን፣ ሁሉም ተወረረ፣
የግለሰቦች ቤት፣ ክብር ተደፈረ፣
በባል ሬሳ ላይ፣ የሚስት ተደመረ፣
ኢትዮጵዩያዊነት በኢትዮጵያ ቀረ!

የቅንጅትንም፣ መሪዎች በሙሉ፣
የሕዝብ ድምጽ ይከበር! ያሉትንም ሁሉ፣
ገብረው ከበሉ፣ ጥቂቶች በስተቀር፣
ከርቼሌ ላካቸው፣ በጨዋታው ሲያፍር፣
በዘር ማጥፋትና፣ ሀገርን በመካድ፣
ከሃዲ ከሰሰው፣ ሁሉን አገር ወዳድ፣
አዬ ዴሞክራሲ!? ደላጎ በገመድ!!?

ምዕራባዊያኑ፣ ሀቁን አውቀውታል፣
ወኪሎቻቸውም፣ ግፉን አይተውታል፣
ማን እንዳቸነፈ፣ በደንብ ያውቃሉ፣
ሀቁን ለማዋጥ ግን፣ ገና ያኝካሉ፣
ሞታችሁ በመኖር፣ ተማሩ ይላሉ።
የሕዝቡን ድል ክደው፣ ወያኔን አውቀዋል፣
ሀቁን ቢረዱትም፣ ሸንገላን መርጠዋል፣
"የድጎማ በጀት፣ ለመንግስት አንሰጥም፣
ለእኛ ወኪሎች ግን፣ ገንዘብ አንነፍግም፣"
በሚል አጉል ሽፋን፣ እያወላወሉ፣
አሁንም በዘዴ፣ ገንዘብ ያፈስሳሉ።

"ልጅን ሲሳስሙ፣ ልጅን ሲያባብሉ፣
እስከነንፍጡ ነው፣" እንደሚባል ሁሉ፣
ወያኔ ኢህአዴግ፣ የስለት ልጃቸው፣
ጠልተው የማይጠሉት፣ ህፃን ሆኖባቸው፣
እስከለሃጩ ነው፣ መሳም የሚሻቸው።

EthioLion.com

እነ አና ጎሜዝ፣ በግልጽ ሲናገሩ፣
የምዕራቡ ነገር፣ ብዙ ነው ምስጢሩ፣
ያ የግንቦት ምርጫ፣ ድርና ማግ ክሩ።
በዴሞክራሲ ዓለም፣ በጠፋበት ውሉ፣
የቁርጥ ቀን ልጆች፣ እስረኞች በሙሉ፣
በጲላጦስ ችሎት፣ ስንቶቹ ተጉላሉ፣
መዳረሻቸውም፣ ላመታት የጠፉ፣ ጭራሽ ያልታዩ አሉ፣
ትላንትን በዛሬ፣ ለሚያስተውል ሁሉ፣
ታሪኩ ይኸው ነው፣ ዘንድሮስ ምን ትሉ?!

የምርጫ ቦርድ መራጭ፣ በሆነበት አገር፣
አንዱ ሰው ፓርላማ፣ በሆነበት አገር፣
ሰላም ዴሞክራሲ፣ አይችልም ሊዳብር።
በሕብረት፣ በአንድነት፣ ወገኖች ታገሉ፣
“ነገ ለራሱ ያውቃል፣ ለነገ አትበሉ፣”
በረባ ባልረባው፣ አትከፋፈሉ፣
በግልጽ ተወያዩ፣ በፍቅር ተቻቻሉ፣
ለብሄራዊ እርቅ፣ መረዋ ደውሉ፣
ወዳጅ ላይሆን ጠላት፣ ግን አትጃጃሉ፣
ወያኔን ከስሩ፣ ነቅላችሁ መንግሉ!

EthioLion.com